የሰ/መ/ቁ. 120355

ሕዳር 06 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

አብዬ ካሳሁን

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- ወ/ሪት ሐናን እስማኤል አብዱልዋሂድ ጠበቃ ወርቁ መንገሻ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- የለም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለጉዳዩ መቅረብ ምክንያት የሆነው አዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 24125 መስከረም 14 ቀን 2008 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ዳኝነት መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ታይቶ ሊታረምልኝ ይገባል በማለት አመልካች በጠበቃቸው አማካኝነት ህዳር 13 ቀን 2008 ዓ.ም የተፃፈ 04 ገጽ የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የአመልካች የሥር አቤቱታ ይዘት በአጭሩ፡-ታህሳስ 10 ቀን 1987 ዓ.ም ከአባታቸው ከአቶ እስማኤል አብዱልዋህድና ከእናታቸው ከወ/ሮ ሳባ አልታሰብ አርባ ምንጭ ከተማ ውስጥ ተወልደው ስማቸው ሐናን እስማኤል አብዱልዋሂድ በሚል ተፅፎ የምስክር ወረቀት ማግኘታቸውን፤ በኋላም የእናታቸው ወንድም ሚስት የሆኑት ወ/ሮ መአዛ አዳነ አሻሜ ሮሆቦት አካዳሚ በተባለው ት/ቤት ሲያስመዘግቡ ሀና አዳነ አሻሜ በሚል ስም ያስመዘገቧቸውና በሂደትም በዚህ ስም የልደት የምስክር ወረቀት የወጣላቸው መሆኑን፤ ከዚያም ወደ ወላጆቻቸው አካባቢ በመመለስ አስቀድሞ በወጣላቸው ሐናን እስማኤል አብዱልዋሂድ በተባለው ስማቸው እየተጠሩ የቀበሌ አስተዳደር መታወቂያ ወጥቶላቸውና አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲም ተመዝግበው እየተማሩ እንደሚገኙ ገልፀው የስማቸው መጠሪያ በተለያየ አጋጣሚ በተለያየ ስም የተመዘገበ በመሆኑ

ችግር ያስከተለባቸው መሆኑን በመጥቀስ ሐናን እስማኤል አብዱልዋሂድ ተብለው እንዲጠሩ እንዲወሰንላቸው አቤቱታ አቅርበው ነበር፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች በትክክለኛው ወላጅ አባታቸው በአቶ እስማኤል አብዱልዋሂድ ስም ልጠራ ያሉ በመሆናቸው ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት ልጅነትን አረጋግጠው ይቅረቡ በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የይግባኝ ቅሬታ በኋላም የሰበር አቤቱታ አቅርበው የነበሩ ቢሆንም ተቀባይነት አላገኙም፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ የቀረበው የሥር ፍርድ ቤቶች ዳኝነት መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል በሚል ሲሆን አቤቱታቸው በአጭሩ፡ የአመልካች አቤቱታ የማንንም ጥቅምና መብት የማይነካ፤ በአሳማኝ ማስረጃም ተደግፎ የቀረበ ሆኖ እያለ የሥር ፍርድ ቤቶች ከውልደቴ ጀምሮ በወጣልኝ ስም ለመጠራት ያቀረብኩትን አቤቱታ ውድቅ ያደረጉት ያላግባብ በመሆኑ ሊታረምልኝ ይገባል  በሚል ያቀረቡት ነው፡፡

ሰበር አጣሪው ችሎቱም መዝገቡን መርምሮ የሥር ፍርድ ቤቶችን ዳኝነት ተገቢነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ በመወሰኑ በጉዳዩ ላይ ተጠሪ የሆነ ተከራካሪ ባለመኖሩ መዝገቡ ለምርመራ የቀረበ ነው፡፡

ክርክሩ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ተጠናቋል፡፡ እኛም አቤቱታው ለሰበር ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አንጻር ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመረነው ምላሽ ማግኘት ያለበት ነጥብ አመልካች በወላጅ አባታቸው እስማኤል አብዱልዋሂድ ስም መጠሪያቸው እንዲሆን የአቀረቡትን አቤቱታ የሥር ፍርድ ቤቶች ውድቅ ያደረጉበት አግባብ ተገቢ ነውን? የሚለው ጭብጥ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በፍትሐብሔር ህግ አንቀጽ 32(1) ሥር በመርህ ደረጃ እንደተመለከተው አንድ ሰው የቤተዘመድ ስም፤ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የግል ስሞች እና የአባት ስም እንደሚኖረው ተደንግጓል፡፡ ለልጁ አባት ስም የሚሆነውም የአባቱ የግል ስም ለመሆኑ በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 36 ሥር ተመልክቷል፡፡ ስለ ልጅ መወለድ መግለጫ ሊሰጥ የሚገባው ሰው ልጁ ከተወለደበት ቀን አንስቶ በዘጠና ቀናት ውስጥ ለልጁ የተሰጠውን የግል ስም ልጁ በተወለደበት ቀበሌ ለሚገኘው የክብር የመዝገብ ጽ/ቤት መግለጫ የማቅረብ ግዴታ የተጣለበት ለመሆኑም ከፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 37 መገንዘብ የሚቻል ነው፡፡ በዚህ ረገድ አመልካች ተወልድኩ በሚሉበት በ1987 ዓ.ም በአገራችን ልደት ጋብቻና ሞት የሚመዘገብ የክብር መዝገብ ሹም በህግ አግባብ ተቋቁሞ በተደራጀ መልኩ ሥራ ላይ ያልነበረ በመሆኑ የአንድ ሰው ስምን በተመለከተ ተደራጅቶ የተጻፈ ማስረጃ

ማግኘት አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ በመሆኑም አመልካች በተወለዱበት ወቅት ልደትን፣ሞትንና ጋብቻን ባግባቡ መዝግቦ ለመያዝ የሚችል የተደራጀ አካል ባለመኖሩ በወላጆች የወጣላቸው ስም በአጎታቸው ሚስት አማካኝነት ተለውጦ በተለያዩ ጊዚያት በተለያዩ ስሞች መጠራታቸውንና የአባታቸውም ስም በተወለዱበት ጊዜ በሆስፒታሉ የምስክር ወረቀት የሰፈረውና በአሁኑ ጊዜ በቀበሌ መታወቂያቸውና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተመዝግበው የሚገኘው ለመሆኑ በፍርድ ቤት እንዲነገርላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሥር መዝገቡ ያስረዳል፡፡

አመልካች አሳዳጊያቸው የነበሩት የአጎታቸው ሚስት ባስመዘገቧቸው ሀና አዳነ አሻሜ በሚል ስም ሮሆቦት አካዳሚ ተመዝግበው መማራቸው፣ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርም የልደት ምስክር ወረቀት ማውጣታቸውን ገልፀዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ወደ ተወለዱበት አካባቢ ተመልሰው ሐናን እስማኤል አብዱልዋሂድ በሚል ስም የቀበሌ መታወቂያ በማውጣት እስከ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተመዝግበው እየተማሩ እንደሚገኙና ይህ ስማቸው አስቀድሞ በተወለዱበት ጊዜ የወጣላቸውና በሆስፒታሉ ምስክር ወረቀት የተመዘገበ ለመሆኑ እየተከራከሩ ይገኛሉ፡፡

አንድ ሰው የቤተዘመድ ስም እንዲለወጥ የመጠየቅ መብት ያለው መሆኑን በዚህ ረገድ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን ፍርድ ቤቶች በሶስተኛ ወገኖች ላይ ጉዳት እንዳይደርስ በጥንቃቄ በመመርመር ስሙን ለመለወጥ በቂ ምክንያት ሲኖር መለወጥ እንደሚችሉ በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 42 ሥር የተደነገገ ሲሆን በዚሁ ህግ አንቀጽ 43 ሥር ደግሞ አንድ ሰው የግል ስሙ እንዲለወጥ ወይም ከብዙዎች የግል ስሞች አንዱ እንዲሰረዝ፣ ወይም ሌላ ግል ስም እንዲጨመርለት ባለጥቅሙ ጥያቄ ባቀረበ ጊዜ ሊፈቀድለት እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ በዚህ ረገድ የሚቀረቡ ጥቄዎችን ፍርድ ቤቶች የአመልካቾችን ስም በማስተካከል ሊወስኑ እንደሚገባቸው የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 87420 ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ ያደረጉበት ምክንያት ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት ልጅነት ሳይረጋገጥ የአባትን ስም መለወጥ አይገባንም በሚል መነሻ ለመሆኑ ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡ አመልካች የጠየቁት ዳኝነት ስሜ ሐናን እስማኤል አብዱልዋሂድ ለመሆኑ የሚያመለክቱ ማስረጃዎች ያሏቸው መሆኑን በመግለፅ በተወለዱበት ጊዜ በዚህ ስም ተጠርተው እንደነበርና በሂደት የአጎታቸው ሚስት በአሳዳጊነት ዘመናቸው ስማቸውን የለወጡባቸው መሆኑንና በኋላም ሲወለዱ ወደ ወጣላቸው ስም ተለውጦ እየተጠሩበት እንደሚገኝ ይህንን የሚያስረዱ ማስረጃዎች መኖራቸውን በማጣቀስ እየተከራከሩ ይገኛሉ፡፡ ስለሆነም ዋናውና መጣራት ያለበት ነጥብ አመልካች በፍሬ ጉዳይነት የሚያነሱት በየጊዜው በተለያዩ ስሞች የመጠራት ወይም ያለመጠራት ጉዳይ ሊሆን ይገባል እንጂ የአመልካች ወላጅ አባት ማን ነው የሚል ጭብጥ ሊሆን አይችልም፡፡ ክርክሩ ያስነሳውን ጭብጥ ፍርድ ቤቶች ምላሽ በሚሰጡበት

ጊዜ የሶስተኛ ወገኖችን ጥቅም እንዳይጎዳ ተገቢ ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የሌላን ሰው ስም ያላግባብ የሚጠቀም ወገን ካለም ህጉ ኃላፊነትን የሚያስከትል ለመሆኑ የደነገገው በመሆኑ ስም ይለወጥልኝ በሚል ጥያቄ የሚያቀርብም ወገን ጥንቃቄ ማድረግ የሚገባው ነው፡፡ በመሆኑም የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች ጉዳይን ከቀረበው የዳኝነት ጥያቄ አንፃር በመመልከትና በአዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41(1)(ሰ) መሠረት በመቀበል የአመልካችን ስም መለወጥ አስፈላጊ የሚያደርጉ ሁኔታዎች መኖር አለመኖራቸውን በማስረጃ አጣርተውና የሶስተኛ ወገን ጥቅም የማይጎዳ ለመሆኑ ጭምር ካረጋገጡ በኋላ ተገቢውን መወሰን ሲገባቸው ጉዳዩን ከልጅነት ይረጋገጥልኝ ጥያቄ አንፃር በመመልከት ውድቅ ማድረጋቸው አግባብነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም የሚከተለውን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 4332/07 ሐምሌ 01 ቀን 2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ፤የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 24075 ነሐሴ 11 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ እንዲሁም የአዲስ አበባ ከተማ ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 24125 መስከረም 14 ቀን 2008 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የአመልካች ጥያቄ የሥም ለውጥ ስለሆነ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤት በአዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41(1)(ሰ) መሠረት ስልጣን አለው ብለናል፡፡ ጉዳዩን የማየት ሥልጣን አለው ብለናል፡፡
3. በመሆኑም የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ስማቸው እንዲለወጥላቸው ያቀረቡትን አቤቱታና ማስረጃ አስቀርቦ በመመርመር የአመልካች ስም መለወጥ በሶስተኛ ወገኖች መብት የሚያስከትለው ጉዳት መኖር አለመኖሩን ጭምር ካጣራ በኋላ ተገቢውን እንዲወስን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 341(1) መሠረት መልሰናል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. በዚህ ችሎት ክርክር የወጣ ወጭና ኪሳራ አመልካች የራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ት/ጌ